# የዲሲ የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ ዳይሬክተር ለመሆን

## የብቁነት መስፈርቶች

ከዲሴምበር 2022 ጀምሮ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ፈቃድ ያለው የልጅ እድገት ማዕከል ውስጥ ዳይሬክተር የሆነ ሰው ከታች ያሉ **ሁለቱን** መስፈርቶች ማሟላት አለበት፦

1. **በቅድመ ልጅነት ትምህርት በ15 የሴምስቴር ክሬዲት ሰዓታት**የባችለር ዲግሪ (የመጀመሪያ ዲግሪ) (ወይም ከዚያ በላይ) ባለቤት መሆን፤ **እና**
2. ከልጆች ጋር በመስራት የአንድ ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት የስራ ልምድ

ሰንጠረዥ 1 አሁን ያለውን የልጅ እድገት ተቋም ዳይሬክተሮች የትምህርት መስፈርትን በዲሴምበር 2022 ውስጥ ተግባራዊ ከሚሆነው አዲሱ መስፈርት ጋር ያነጻጽራል።

**ሰንጠረዥ 1**

| የሚያስፈልገው ያሁኑ የትምህርት የምስክር ወረቀት | በዲሴምበር 2022 የሚያስፈልገው አዲስ የትምህርት የምስክር ወረቀት |
|---|---|
| • በቅድመ የልጅነት ትምህርት (ኤርሊ ቻይልድሁድ ኢዱኬሽን) ወይም የቅድመ ልጅነት እድገትን በዋናነት የሚያጠና ተባባሪ ዲግሪ እና የሶስት ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት የስራ ልምድ<br>**ወይም**<br>• በቅድመ ልጅነት ትምህርት 15 ክሬዲት ሰዓታት ያላቸው 48 የሴምስቴር ክሬዲት ሰዓታት | • የመጀመሪያ (ባችለር) ዲግሪ በቅድመ ልጅነት ትምህርት፣ የቅድመ ልጅነት እድገት፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ወይም የቀደመ የልዩ ፍላጎት ትምህርት<br>**ወይም**<br>• በቅድመ ልጅነት ትምህርት ቢያንስ የ15 የሴምስቴር ክሬዲት ሰዓታት ያለው በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ የባችለር ዲግሪ (የመጀመሪያ ዲግሪ) |

እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት ድጋፍ ካስፈለገዎ፣ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (ኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን) (OSSE)፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዩኒቨርሲቲ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ሌሎች ኮሌጆች እና የህብረተሰብ ድርጅቶች ዲግሪ እንዲያገኙ የሚያግዙዎት የተለያዩ[የስልጠና እና የስኮላርሺፕ ፕሮግራሞችን](#) ያቀርባሉ። እርስዎ አሁንም ትምህርትዎን እየተማሩ ከሆነ ወይም ካልሆነ እስከ ዲሴምበር 2022 መስፈርቶቹን ሙሉ በሙሉ የማያሟሉ ከሆነ፣ ለአጠቃላይ መታለፍ ማመልከት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ላለፉት 10 ዓመታት (ከዲሴምበር 2006 ወይም ከዚያ በፊት ጀምረው) በተመሳሳይ (ወይም ተነጻጻሪ) ሚና/የስራ መደብ ላይ በአገልግሎት ላይ ጉልህ ክፍተት ሳይፈጥሩ በቀጣይነት አገልግለው ከሆነ፣ ለ [10-ዓመት ተከታታይ አገልግሎት መታለፍማመልከት ይችላሉ።](#)

እባክዎ መታለፎች በጉዳይ-ለጉዳይ መሰረት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ እና ዋስትና እንደሌላቸው ያስተውሉ—ስለዚህ በተገኙ የትምህርት እድሎች እንዲጠቀሙ በጥብቅ እናበረታታዎታለን።

የግል እቅድ ለማዘጋጀት እርዳታ ካስፈለገዎ ወይም እንዴት እንደሚጀምሩ እርግጠኛ መሆን ካልቻሉ፣ የECE እርዳታ-ሰጪ የፊት ወንበር ላይ የተቀመጠውን ሰው ያነጋግሩ። ድጋፎች በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

### እኛ ድጋፍ ለመስጠት እንገኛለን!

የECE እርዳታ-ሰጪ የፊት ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው የመገኛ መረጃ፦ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903

| በአስፈላጊነት የሚገኝ | በቀጠሮ |
|---|---|
| ይደውሉ ወይም ኢሜይል ይላኩ እና ምላሽን ወዲያውኑ ወይም በ24 ሰዓታት ውስጥ ይቀበሉ | የግል የመገኘት ሁኔታዎ ላይ በመመርኮዝ ለግላዊ እቅድ ቀጠሮ ለመያዝ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ይላኩ |